Washington State Department of
Labor & Industries







# ገለልተኛ የሕክምና ምርመራዎ

## የገለልተኛ ሕክምና ምርመራ (Independent Medical Exams, IMEs) በማስመልከት ከሚቀርቡት የተለመዱ ጥያቄዎችውስጥ የተወሰኑንትን ይመልሱ

### ለምንድነው የህክምና ምርመራ እንዳደርግ እቅድ የተያዘልኝ?

እርስዎ የሕክምና ምርመራ እንዲያደርጉ እቅድ የተያዘበት ምክንያት የስራቦታ ላይ ላጋጠመዎ ጉዳት ወይንም ስራ ላስከተለብዎ በሽታ ተገቢ ህክምና እንዲያገኙ ለማድረግ ነው። የሕክምና ምርመራዎች ለሚከተሉት አላማዎች ያስፈልጋሉ:

- ሐኪምዎ፣ አሰሪዎ ወይንም የካሳ ጥያቄ ሀላፊዎ የጤና ሁኔታዎ እንዲፈተሽ ሲጠይቁ።
- የጉዳትዎ መጠን መገምገም ስንፈልግ።
- ለእርስዎ የሚያስፈልገው የሕክምና አይነት እና ሕክምናው የሚፈጀው ጊዜ በተመለከተ ጥያቄ ሲነሳ።
- እርስዎ የካሳ ጥያቄዎ እንዲዘጋ፣ እንደገና እንዲከፈት ወይንም እንዲፈቀድ ሲጠይቁ።
- የካሳ ጥያቄዎ በተመለከተ ባስተላለፍነው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ከጠየቁ ወይንም እንደገና እንድናይልዎ ጥያቄ ሲያቀርቡ።

### የሕክምና ምርመራውን በተመለከተ እንዴት ነው የሚነገረኝ?

የሰራተኞች እና የኢንዳስትሪዎች መምሪያ (L&I) ምርመራዎ የት እና መቼ እንደሚከናወን የሚገልጽ ደብዳቤ ቢያንስ ምርመራው ከሚካሄድበት ቀን 14 ቀናት አስቀድሞ ይልክልዎታል። ቀጠረዎ አክብረው የመገኘት ሀላፊነት አለብዎ።

### የምርመራየ ቀጠሮ መቀየር ብያስፈልግስ?

ምርመራዎ ለመቀየር የሚያስችል ብቁ ምክንያት ካለዎት እና ለሰራተኞች እና ኢንዳስትሪዎች መምሪያ በበቂ ሁኔታ ካሳወቁ፣ የካሳ ጥያቄዎ ላይ የሚፈጠር ችግር አይኖርም።

የምርመራ ቀጠሮው(ዎች) አስፈላጊ ስፔሻሊስቶች ባሉበት እና ለእርስዎ አመቺ በሆነ ቦታ እንዲሆን መምሪያው የቻለውን ሁሉ ያደርጋል። ምርመራ የሚካሄድበት ቀጠሮ ወይንም ቦታ በተመለከተ የሚያሳስብዎ ነገር ካለ፣ ምርመራው ከሚካሄድበት ቀን ቢያንስ ከአምስት የስራ ቀናት በፊት ሊያሳውቁን ይገባል።

ቀጠሮ ለማስቀየር ደብዳቤው ላይ ባለው ስልክ ቁጥር ወይንም ወደ IME የቀጠሮ ክፍል ይደውሉ፣ 1-800-468-7870።

### ለምርመራው መክፈል ይጠበቅብኛል?

እርስዎ ምርመራው ላይ ከተገኙ እና የሚጠበቅብዎትን ትብብር ካደረጉ ማናቸውም ለሚርመራው ወጪ የሚደረጉ ክፍያዎች የሰራተኞች እና ኢንዳስትሪዎች መምሪያ ይሸፍናል። ያለ ብቁ ምክንያት ምርመራው ላይ ሳይገኙ ከቀሩ፣ ከጊዜ ኪሳራ አበሎችዎ ላይ የምርመራ ወጪው ተቀናሽ ሊደረግ ይችላል። ሌሎች ጥቅማጥቅሞችንም ሊያጡ ይችላሉ።

### ምርመራውን የሚያካሂደው ማነው?

ሐኪም ነው ምርመራ የሚያደርግልዎ። በአንዳንድ አጋጣሚዎች ምርመራውን ወይንም ተከታታይ ምርመራዎችን በብዙ ሐኪሞች ሊከናወኑ ይችላሉ።

### ጓደኛየ ወይንም ዘመዴ ወደ ምርመራው ይዤ መምጣት እችላለሁ?

አዎ፣ ነገርግን እሱ ወይንም እሰዋ ክፍያ ሊከፈላቸው ወይንም ወጪዎቻቸው ሊወራረዱላቸው አይችሉም። የአእምሮ ምርመራ ከሆነ የሚደረግልዎ፣ አብረዎት የመጣ ሰው ወደ ምርመራ ክፍሉ መግባት አይችልም።

ከእድሜ በታች የሆነ ህጻን ወደ ገለልተኛ ሕክምና ምርመራው (IME) ይዘው መምጣት አይችሉም።

### ወደ ምርመራው ኤክስ-ሬይ፣ ኤምአርአይ፣ ወይንም ሲቲ ስካን ይዤ እንድመጣ ከተነገረኝስ?

ኤክስ-ሬይ፣ ኤምአርአይ፣ ወይንም ሲቲ ስካን ለማድረግ እገዛ ካስፈለገዎት፣ የሐኪምዎን ጽሕፈት-ቤት ያናግሩ።

## ምርመራው ላይ ምንድነው የሚደረገው?

መርማሪ ሐኪሙ ከካሳ ጥያቄዎ ጋር ተያያዥ የሆኑትን ችግሮች ብቻ ይመረምራል፣ ስለ ሕክምናዊ ታሪክዎ ይጠይቅዎታል፣ እና የካሳ ጥያቄ ፋይልዎ ላይ የሚገኘውን የሕክምና መረጃ ይገመግማል። ወደ የግል ሐኪምዎ ሄደው የህክምና እርዳታ ማግኘት እንዳለብዎ ሊመክርዎ ይችላል፣ ራሱ ግን አያክምዎትም።

ምርመራዎ አጭር ሊሆን ይችላል። ሙሉ አካላዊ ምርመራ ይደረግልኛል ብለው መጠበቅ የለብዎትም። ይሁን እንጂ፣ በአንዳንድ አጋጣሚዎች ሙሉ ምርመራ፣ የላቦራቶሪ ምርመራዎች እንዲሁም ኤክስ-ሬይ ጭምር ሊካተቱ ይችላሉ። ይህ የመርማሪ ሐኪሙ ውሳኔ ይሆናል።

## በምርመራው ምክንያት ከስራ የምቀር ከሆነ፣ የደሞዝ ኪሳራየ እንዴት ነው የሚከፈለኝ?

መምሪያው ያዘጋጀው የገለልተኛ ሕክምና ምርመራ ለማድረግ ከ 30 ደቂቃ በላይ (ያለክፍያ) ከስራዎ ለመቅረት የሚገደዱ ከሆነ፣ ከስራ ለቀሩባቸው ሰአታት ካሳ ሊከፈለዎ ይችላል። በምርመራው ምክንያት ከስራ ውጪ ለሚያጠፉት ጊዜ በሰአት በሚያገኙት ክፍያ ተሰልቶ ካሳ ይከፈለዎታል። እባክዎ በአባሪነት የቀረበው ቅጽ ይመልከቱ፣ *የገለልተኛ ሕክምና ምርመራ የጉዞ እና ደሞዝ ማካካሻ መጠየቂያ*።

## የጉዞ ወጪዎቼን የሚሸፍንልኝ ማነው?

ብዙ ግዜ፣ የሰራተኞች እና ኢንዳስትሪዎች መምሪያ ነው የጉዞ ወጪዎችን የሚሸፍነው። አስፈላጊ ከሆነ ደግሞ፣ ምግቦች፣ የሆቴል ወጪዎች፣ የታክሲ ክፍያ፣ የተሽከርካሪ ማቆምያ ወጪ፣ የማሻገርያ ጀልባ እና የድልድይ ክፍያ በመምሪያው የወቅቱ ተመን መሰረት ይከፈላሉ። እባክዎ የወጪዎችዎን ደረሰኝ ይቀበሉ።

ወደ ምርመራዎ በአውሮፕላን፣በባስ ወይንም በባቡር ከሆነ የሚጓዙት፣ ከገለልተኛ ሕክምና ምርመራ የቀጠሮ ክፍል ጋር ይነጋገሩ፣ 1-800-468-7870። የሰራተኞች እና ኢንዳስትሪዎች መምሪያ ለጉዞዎ አስፈላጊ ነገሮችን ያመቻችልዎታል።

## የጉዞ ወጪዎቼን ማካካሻ እንዴት ነው የሚከፈለኝ?

ምርመራ ካደረጉበት ጊዜ አንስቶ በአንድ አመት ውስጥ የማካካሻ ክፍያ መጠየቂያ ቅጹ ሞልተው ከደረሰኞችዎ ጋር አያይዘው ማቅረብ አለብዎ። ቅጹ ላይ ፊርማዎን ማኖር አለብዎ። (የቅጹ መመሪያዎችን ይመልከቱ)

## ከጉዞ ሊያግደኝ የሚችሉ የአእምሮ ወይንም የአካል ጉዳት ካሉብኝስ እንዴት ነው ወደ ሕክምና ምርመራው መሄድ የምችለው?

ወደ ምርመራ ለመሄድ የሚያስችልዎ ዝግጅት እንዲደረግልዎ፣ በስልክ ቁጥር 1-800-468-7870 የገለልተኛ ሕክምና ምርመራ ክፍልን ያነጋግሩ። የአእምሮ ወይንም የአካል ጉዳቱ ከካሳ ጥያቄዎ ጋር መያያዝ የለበትም።

# የቅጹ መመሪያዎች

እባክዎ ቅጹን በጥንቃቄ ይሙሉ። ያልተሟላ ወይንም የተሳሳተ መረጃ ካስረከቡን፣ ቅጹን እንዲያስተካክሉት ልንመልስልዎ እንችላለን። የተሞላው ቅጽ እና ደረሰኞችዎ ወደሚከተለው ይላኩ:

Department of Labor & Industries
PO Box 44269
Olympia, WA 98504-4269

### ተጨማሪ እርዳታ እንዴት ማግኘት እንዳለብዎ እዚህ ይዩ

ቀጠሮ ስለተያዘለት ምርመራዎ ጥያቄ ካለዎት፣ እባክዎ ከሰራተኞች እና ኢንዳስትሪዎች መምሪይ የቀጠሮዎች ክፍል ጋር በስልክ ቁጥር 1-800-468-7870 ደውለው ይነጋገሩ።

የምርመራ ተመኩሮዎ በተመለከተ አስተያየቶችዎ ሊልኩልን ከፈለጉ፣ በስልክ ቁጥር 1-888-784-8059 ወደ የገለልተኛ ሕክምና ምርመራ መስመር መደወል ይችላሉ።

የካሳ ጥያቄዎ በተመለከተ ተጨማሪ ጥያቄዎች መጠየቅ ከፈለጉ እባክዎ በስልክ ቁጥር 1-800-547-8367 ወደ የመረጃ እና የእገዛ ጽሕፈት-ቤታችን ይደውሉልን።

የሰራተኞች እና ኢንዳስትሪዎች መምሪያ ድረገጽን ይጎብኙ:
www.Lni.wa.gov

በሚቀርብልን ጥያቄ መሰረት፣ የውጭ ቋንቋ እገዛ እና አቀራረቦችን የአካል ወይንም የአእምሮ ጉዳት ላለባቸው ሰዎች እናቀርባለን። ይደውሉ 1-800-547-8367። የ TDD ተጠቃሚዎች፣ በ 360-902-5797 ይደውሉ። የሰራተኞች እና ኢንዳስትሪዎች መምሪያ የእኩል እድል ቀጣሪ ነው።

PUBLICATION F245-224-201 (Amharic) [02-2014]

**የተሞላውቅጽወደሚከተለውይላኩ:**
Department of Labor and Industries
PO Box 44269
Olympia WA 98504-4269

# የገለልተኛሕክምናምርመራ (IMEs)
# IME የጉዞእናደሞዝማካካሻክፍያመጠየቂያቅጽ

- ከመጀመርዎ በፊት ከጀርባ ያሉትን መመሪያዎች ያንብቡ።
- ለገለልተኛ ሕክምና ምርመራ ሳይሆን ለሌላ አላማ ከሆነ የሚጓዙት፣ የጉዞ ወጪ ማካካሻ ክፍያ መጠየቂያ ቅጽ (F245-145-000) ነው መጠቀም ያለብዎ።

## የሰራተኛ መረጃ

| | |
|---|---|
| | የካሳ ጥያቄ ቁጥር |
| ስም (የመጨረሻ፣ የመጀመሪያ፣ የመካከለኛ መነሻ) | ጉዳት የደረሰበት ቀን |
| የሰራተኛ ቤት አድራሻ (የፖስታ ሳጥን ቁጥር አይደለም) | የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር (ለመታወቂያ ብቻ) |
| ከተማ ስቴት ዚፕ ኮድ | የሰራተኛው ስልክ ቁጥር |

## የጉዞ መረጃ – መመሪያዎች እና ምሳሌ ከጀርባ ይመልከቱ።

| | A. የእያንዳንዱ ጉዞ ቀን (ወር-ቀን-አመት) | B. የጉዞ ኮድ (በአንድ መስመር አንድ – የቅጹ ጀርባ ይመልከቱ) | C. ከ (ከተማ) | D. ወደ (ከተማ እና የመረመርዎ ሰው) | E. ስንት ማይል (የደርሶመልስ) | F. ወጪ (በአንድ መስመር አንድ) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | | | | | | $ |
| 2. | | | | | | $ |
| 3. | | | | | | $ |
| 4. | | | | | | $ |
| 5. | | | | | | $ |
| 6. | | | | | | $ |
| 7. | | | | | | $ |
| 8. | | | | | | $ |

## ደሞዝ ማወራረድ:

መምሪያው ያዘጋጀው የገለልተኛ ሕክምና ምርመራ ለማድረግ ከ 30 ደቂቃ በላይ ***ያለክፍያ*** ከስራዎ ለመቅረት የሚገደዱ ከሆነ፣ ከስራ ለቀሩባቸው ሰአታት ካሳ ሊከፈለዎ ይችላል። በገለልተኛ ሕክምና ምርመራው ምክንያት ከስራ ውጪ ለሚያጠፉት ጊዜ በሰአት በሚያገኙት ክፍያ ተሰልቶ ይወራረድልዎታል። እባክዎ ጠቅላላ ሰአቱ እና ደሞዝ ከታች ይሙሉ፣ ከዛ የጉዞ ኮድ 0411A በመጠቀምመረጃውንከላይባሉትመስመሮችላይያስፍሩ።

የገለልተኛ ሕክምና ምርመራ ለማድረግ የጠፋው ጊዜ: ____ ሰአት ____ ደቂቃ። የገለልተኛ ሕክምና ምርመራ ለማድረግ ባጠፉት ጊዜ በሰአት ሊያገኙት የነበረው ደሞዝ: $_____

| | |
|---|---|
| የአሰሪ ስም | የአሰሪ ስልክ ቁጥር |
| የአሰሪ አድራሻ ከተማ ስቴት ዚፕ | |

## የሰራተኛው ፊርማ – ያልተፈረሙ ቅጾች ተመላሽ ይሆናሉ።

እነዚህ ወጪዎች ከሰራተኛየ የካሳ ጥያቄ ጋር የተያየዙ ሲሆኑ ገና ያልተወራረዱ ናቸው። እያወቁ የውሸት መረጃ ማቅረብ ወንጀል መሆኑን አውቃለሁ።

በቅጹ ጀርባ ላይ ያሉት መመሪያዎች እንዳነበብኳቸው እንደተረዳሁዋቸው እገልጻለሁ።

| | |
|---|---|
| የሰራተኛ ፊርማ | ቀን |

# IME የገለልተኛ ሕክምና ምርመራ የጉዞ ወጪ ማካካሻ መጠየቂያ ቅጽ ለመሙላት የተዘጋጁ መመሪያዎች:

ይህንን ቅጽ ለገለልተኛ ሕክምና ምርመራ ጉዞ ብቻ ይጠቀሙበት። ለሌላ አላማ ለሚያደርጉት ጉዞ፣ የግድ ሌላ ቅጽ ነው መጠቀም ያለብዎ። ይህንን ቅጽwww.Lni.wa.gov/forms/pdf/F245-145-000.pdfላይ መሙላት ይችላሉ።

ይህንን ቅጽ ምርመራ ካደረጉበት ቀን አንስቶ በአንድ አመት ውስጥ መሙላት አለብዎ።

**እያንዳንዱን ረድፍ ይሙሉ:**

- **ረድፍ A:**የተጓዙበት ቀን (አንድ ቀን በአንድ መስመር)።
- **ረድፍ B:**የጉዞ ኮድ። ትክክለኛውን ኮድ ከታች ካለው ዝርዝር ያግኙ። አንድ ኮድ በአንድ መስመር ብቻ።
- **ረድፍ C:** የጉዞ መነሻ ከተማ።
- **ረድፍ D:** የጉዞ መዳረሻ ከተማ።
- **ረድፍ E:**ዶርሶመልስ የተጓዙበት ጠቅላላ ርቀት በማይል። ከሁሉም ያጠረው መስመር ከቤትዎ ያለው ርቀት ላይ በመመስረት በወቅታዊ የጉዞ ርቀት ክፍያ መጠን ተሰልቶ ይከፈልዎታል።
- **ረድፍ F:** የእያንዳንዱ ወጪ መጠን በዶላር። አንድ ወጪ በአንድ መስመር። ሁሉንም ደረሰኞች በአባሪነት መላክ አለብዎ። ሁሉንም ደረሰኞች የተቆጠሩ እና ተነባቢ መሆን አለባቸው። የክሬዲት ካርድ ስሊፖች አያስፈልጉም። ከ $10 በታች የሆኑ የመኪና ማቆሚያ ወጪዎች ደረሰኝ አይጠየቅባቸውም።

**የጉዞ ኮድ:**

| ወጪ | የጉዞ ኮድ |
|---|---|
| ያልተከፈለበት የስራ ሰአት (ሰአት x ደሞዝ) | 0411A |
| የግል ተሽከርካሪ የተጓዘበት ርቀት | 0412A |
| የተሽከርካሪ ማቆሚያ | 0402A |
| የድልድይ እና የመሻገሪያ ጀልባ ወጪ | 0403A |
| የንግድ ማጓጓዣ | 0405A |
| ታክሲ | 0414A |
| ማረፊያ | 0406A |
| ቁርስ | 0407A |
| ምሳ | 0408A |
| እራት | 0409A |

**ፊርማ:**
እንዲወራረድልዎ የግድ ቅጹን መፈረም አለብዎ።

**ለምሳሌ:**

| | A. የእያንዳንዱ ጉዞ ቀን (ወር-ቀን-አመት) | B. የጉዞ ኮድ (በአንድ መስመር አንድ – የቅጹ ጀርባ ይመልከቱ) | C. ከ (ከተማ) | D. ወደ (ከተማ እና የመረመርዎ ሰው) | E. የጊዜርቀትበማይል (የደርሶመልስ) | F. ወጪ (በአንድመስመርአንድ) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | 02/14/14 | 0412A | Olympia | Seattle; Dr. Smith | 60 | $ |
| 2. | 02/14/14 | 0408A | | | | $ 20.00 |

**የተሞሉቅጾችንወደሚከተለውይላኩ:**

Department of Labor and Industries
P.O. BOX 44269
Olympia WA 98504-4269